# ከሚልክያስ እስከ ክርስቶስ

410 400 390 380 370 360 350 340 330 320 310 300 290 280 270 260 250 240 230 220 210 200 190 180 170 160 150 140 130 120 110 100 90 80 70 60 50 40 30 20 10 — 10 20 30

## የፋርስ ዘመን 450-330 ዓ.ቅ.ክ

ከነህምያ በኋላ ለ200 ዓመታት የፋርስ መንግሥት ይሁዳን በቍጥጥሩ ሥር አድርጎ ቢቆይም አይሁዶች ግን ሃይማኖታዊ ሥርዐቶቻቸውን ያለ ችግር ያካሂዱ ነበር። በዚህ ጊዜ የይሁዳ ምድር ለአይሁድ መንግሥት ኀላፊነት በነበረው በሊቀ ካህናት ይተዳደር ነበር።

## የታላቁ እስክንድር መንግሥት

## የግሪክ ዘመን 330-166 ዓ.ቅ.ክ

በ33 ዓ.ቅ.ክ በመቄዶንያ ሰፍሮ የነበረው የፋርስ ሠራዊት በታላቁ እስክንድር ተሸነፈ። እርሱም ዓለምን አንድ ሊያደርግ የሚችለው የግሪክ ጠንካራ ባሕል እንደሆነ አመነ። አይሁዶች ሃይማኖታዊ ሥርዐታቸውን እንዲፈጽሙ፣ በሰንበት ዓመት ከግብር ነጻ እንዲሆኑ፣ የእስክንድርያ ከተማን ከሠራ በኋላ አይሁዶች እዚያ እንዲኖሩ በግሪክ ግዛት ሥር ካሉ ሕዝቦች ጋር እኩል መብት ሰጣቸው። የግሪክ ብዙ አገሮች መያዝ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ወደ ግሪክ ቋንቋ እንዲተረጎሙ መንገድ ከፈተ (የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም በ250 ዓ.ቅ.ክ ተተረጐመ)

የግብፁ በጥሉመስ መንግሥት

የሶሪያ መንግሥት ሴሉ ሲድ

## የአስሞኒያን ዘመን 166-63 ዓ.ቅ.ክ

ይህ ታሪካዊ ዘመን ሲጀመር አይሁዳውያን በከፋ ሁኔታ ይጨነቁ ነበር። የበጥሉመስ ገዢዎች የአምልኮ ሥርዐታቸውን እንዲፈጽሙ ፈቅደው ነበር፤ የሴሉሲድ ገዢዎች ግን የግሪክን ባሕል በግድ እንዲከተሉ ያደርጓቸው፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማቃጠል የሕግ ጫና ያበዙባቸው ነበር። የተጨቈኑት አይሁዶች በይሁዳ መቃብያን በመመራት ዐመፁ።

የአስሞኒያን ሥርወ መንግሥት

## የሮም ዘመን 63 ዓ.ቅ.ክ

በ63 ዓ.ቅ.ክ የሮም ጄኔራል ፖምፒ ኢየሩሳሌምን ያዘ፤ የፍልስጥኤም አውራጃዎችም ለሮም ግብር ሆኑ። በአካባቢው የነበረው መንግሥት አንዳንዱን ክፍል ለልዑላን ሌላውን/ ደግሞ ለአገረ ገዢነት በተሾሙ ባለ ሥልጣናት ይተዳደር ነበር። ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን ታላቁ ሄሮድስ በፍልስጥኤም ምድር ሁሉ ላይ ይገዛ ነበር።

ታላቁ ሄሮድስ በሮማ ሥር ሆኖ እንደ ንጉሥ ይገዛ ነበር

- 334 - 323 ታላቁ እስክንድር የምሥራቁን ዓለም ያዘ
- 330 - 328 ታላቁ እስክንድር በሥልጣን የቆየበት
- 320 ቀዳማዊ በጥሊሞስ ኢየሩሳሌምን ያዘ
- 311 ሴሉሲስ ባቢሎንን ያዘ፤ የሴሉሲድ ሥርወ መንግሥት ጀመረ
- 226 የሶሪያው አንጥዮኮስ ሣልሳዊ (ታላቁ) ፍልስጥኤምን ያዘ
- 223 - 187 አንጥዮኮስ የሶሪያ ንጉሥ ሆነ
- 198 አንጥዮኮስ ግብፅን በማሸነፍ ፍልስጥኤምን ያዘ
- 175 – 164 አንጥዮኮስ አራተኛ ኤጲፋኔስ የሶሪያ ንጉሥ ሆነ፤ ይሁዲነት ተከለከለ።
- 167 ማትያስና ልጆቹ በአንጥዮኮስ ላይ ዐመፁ፤ የመቃብያን ዐመፅ ጀመረ።
- 166 - 160 የይሁዳ መቃብያን መሪነት
- 160 - 143 ዮናታን ሊቀ ካህናት ሆነ
- 142 የኢየሩሳሌም ??????????
- 142 - 134 ስምዖን ሊቀ ካህናት ሆነ፤ የአስሞኒያን ሥርወ መንግሥትን መሠረተ
- 134 - 104 ዮሐንስ ሒርካኑስ ነጻ የአይሁድ ግዛትን አስፋፋ
- 103 የአርስጦቡሎስ ግዛት
- 102 - 76 የእስክንድርያ ኢያኔዎስ ግዛት
- 75 - 67 የሰሎሜ እስክንድርያ እና ዳግማዊ ሂርቃኑስ እንደ ሊቀ ካህናት ሆኖ በጋራ ሆነው የገዙት
- 66 - 63 በዳግማዊ አርስጦቡሊስና በዳግማዊ ሂርቃኑስ መካከል የተደረገ ጦርነት
- 63 ፖምፒ ፍልስጥኤምን ወረረ፤ የሮም ግዛት ጀመረ
- 63-40 ዳግማዊ ሂርቃኑስ በሮም ሥር ሆኖ መግዛት ጀመረ
- 40-37 ፓርቲያኖች ኢየሩሳሌምን ያዙ
- 37 ኢየሩሳሌም ለስድስት ወር ተከበበች
- 32 ሄሮድስ ተሸነፈ
- 19 የሄሮድስ ቤተ መቅደስ ሥራ ተጀመረ
- 16 ሄሮድስ አግሪጳን ጎበኘ
- 4 ሄሮድስ ሞተ፤ አርኬላዎስ ተተካ

# በሁለቱ ኪዳናት መካከል የነበረው ዘመን

በሁስቱ ኪዳናት መካከል የነበረው ዘመን፣ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የቈየና ስውጥ የተካሄደበት ዘመን ነው። ይህ ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ለ3000 ዓመት ያህል ተንሰራፍቶ የቈየው ባሕል እየጠፋ፤ የኀይል ሚዛን በአዲስ መልክ እየተዋቀረ የመጣበት ወቅት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፣ ነህምያ በነበረበትና ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን መካከል ያለው (በግምት የ400 ዓመት) ጊዜ፣ በኪዳናት መካከል ያለው ዘመን (432-5 ዓ.ቅ.ክ) በመባል ይታወቃል። አንዳንድ ጊዜ፣ "የዝምታው ዘመን" ተብሎ ይጠራል። ነገር ግን የዚህ ዘመን ሁነቶች፣ ሥነ ጽሑ ፎችና ማኅበራዊ ግንኙነቶች የዘመነ አዲስን ዓለም በእጅጉ ቀርጸውታል።

## ታሪክ

ከባቢሎናውያን ምርኮ የተንሣ እስራኤል ራሷን የቻለች አገር መሆኗ ቀርቶ፣ የታላላቆቹ ዐፄ ግዛቶች ትንሽ ግዛት ሆነች። በኪዳናት መካከል ያለውን ዘመን አስመልክቶ በቀደምት የታሪክ ምንጭነት የሚጠቀሰው አይሁዳዊው ታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን (ጆሴፈስ) ስለ ፋርሶች የጻፈው አንዳች ነገር ባለመኖሩ በዚያ አቅጣጫ የሚታወቅ ብዙ ነገር የለም።

ታላቁ እስክንድር ፓለስቲናን (332 ዓ.ቅ.ክ)የግዛቱ አካል ከማድረጉ የተነሣ እስራኤል አዲ ስና ስውር የሆነ ጥቃት ይደርስባት ጀመረ። እስክንድር ዓለምን በግሪክ ቋንቋና ባህል ሥር የማድረግ ዐ ላማ ያለው ሰው ነበር። 'ሔለናይዜሽን' የተባለው ይህ አስተሳሰብ (ፖሊሲ) እርሱን በተከተሉ ሰዎችም ዘንድ ተቀባይነት ነበረው። ፖሊሲው በተለይ በአይሁዳውያን ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ማስከተሉ አልቀረም።

እስክንድር በ323 ዓ.ቅ.ክ ሲሞት ድል አድርጎ የያዛቸው የዐፄ ግዛቶች፣ ለጦር ጀኔራሎቹ ተከፋፈሉ። ከእነዚህም መካከል ሁለቱ ጀኔራሎች ሥርወ መንግሥት መሠረቱ፤ እነዚህም በግ ብፅ የነገሠው በጥሊሞስና በሶርያና በመስጴጦምያ የነገሠው ሴሉዊሲድ ነበሩ። ይህም ፓለስቲናን ከአንድ ምእተ ዓመት በላይ ለመቈጣጠር ትልቅ ሚና ተጫውቶአል።

የበጥሊሞስ አመራር ለአይሁድ ሃይማኖታዊ ቅናት ስፍራ የሚሰጥ ነበር፤ ነገር ግን በ198 ዓ.ቅ.ክ. ላይ፣ ሴሉዊሲድ አካባቢውን በመቈጣጠር በአይሁድ ታሪክ ውስጥ እጅግ በጣም ከሚታወቁት የጀግንነት ዘመናት መካከል ለአንዱ ጥርጊያ መንገድ ከፈተ።

የመጀመሪያው የሴሉዊሲድ አገዛዝ ዘመን፤ እንደ በጥሊሞስ ሰላም የሰፈነበት ነበር፤ ከ175-164 ዓ.ቅ.ክ ነግሦ የነበረው አራተኛው አንጥያኮስ ኢጲፋኔዎስ ("የተገለጠ እግዚአብሔር") ግን በመፍረክረክ ላይ ያለውን የሔሌናይዜሽን ፖሊሲ እንደ መፍትሔ አድርጎ ተጠቀመበት። የአይሁድ ነገሥታት ቤተ ሰቦች፣ የግሪካውያኑን ልማድ ቀድሞውኑ ገንዘባቸው ቢያደርጉትም፣ በአብዛኞቹ አይሁድ ዘንድ ግን ሔሌናይዜሽን ቍጣን ቀስቅሶአል።

የአንጥያኮስ አመራር ያነጣጠረው የአይሁድን ሃይማኖት በማጥፋት ላይ ነበር። ስለዚ ህም መሠረታዊ የሚባሉ የአይሁድ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶች እንዳይከናወኑ በጥብቅ ከለከለ፤ አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ቅጆች ሁሉ የማጥፋት ሙከራ አደረገ፤ እንዲሁም ሱዝ ስሚባለው የሚመሰክ ጣዖት መሥዋዕት እንዲቀርብ አዘዘ፤ በተለይም የዚህን ጣዖት ምስል ማቆሙና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በሣማ መሠዋቱ ታላቅ ቍጣን ቀሰቀሰ።

በአንጥያኮስ ላይ የተካሄደው ተቃውሞ የተመራው፣ በአንድ ትንሽ መንደር በሚኖረውና ከካህናት ቤተ ሰብ በተወለደው በሽማግሌው ማታቲያስና በአምስት ልጆቹ ነበር። እነርሱም ይሁዳ (መቃቢዮስ)፣ ዮናታን፣ስምዖን፣ዮሐንስና ኤሊዓዘር ይባላሉ። ማታቲያስ ሞዲን በተባለችው የእርሱ መኖሪያ መንደር የተተከለውን የጣዖት መሠዊያ አፈረሰ፤ ከአንጥያኮስ ዘንድ በምስጢር የተላከውንም መልእክተኛ ገደለ። ይህም 24 ዓመት ያዋጋውን (166-142 ዓ.ቅ.ክ) የመቃብያንን ሀመፅ ቀሰቀሰ። ሮማውያን በ63 ዓ.ቅ.ክ አካባቢውን እስከ ተቈጣጠሩበት ጊዜ ድረስም፤ ይሁዳ በማንም ላይ ጥገኛ ሳትሆን መቈየት እንድትችል መንገድ ከፈተ።

የማታቲያስ ቤተ ሰቦች ድል በታላቅ ገድል የተገኘ ቢሆንም እንኳ፣ ከመጨረሻ ልጁ ከስምዖን ሞት በኋላ መሥርተውት የነበረው የሐስሞናውያን ሥርወ መንግሥት ቀስ በቀስ ወደ ንጉሣዊ አስተዳደር ተቀየረ። የሔሌናይዜሽንን አስተዳደር ከሴሉዊሲድ አስተዳደር ለይቶ መመልከት አንዳንዴ አስቸጋሪ ነው። ከስምዖን ልጅ ከዮሐንስ አርቃኔዎስ ንግሥና በኋላ መቃብያንን ይደግፉ የነበሩት ርቱዓን አይሁድ ተቀባይነት እያጡ መጡ። ከጥቂቶቹ በስተቀር ሐስሞናውያን አይሁድ የሔሌናይዜሽን ደጋፊዎች ሆኑ። ፈሪሳውያንም በታላቁ ጃኒ

ዎስ (102-76 ዓ.ቅ.ክ) መስደድ ጀመሩ::

በ63ዓ.ቅ.ክ ላይ የሐስሞናውያን ሥርወ መንግሥት አከተመ:: በመስፋፋት ላይ ያለው የሮማውያን የዐፄ ግዛት በሁለቱ የጃኔዎስ ልጆች፣ ማለትም በዳግማዊ አርስጦቡሎስና በዳግማዊ ሔሪክኔዎስ የሥልጣን ሽኩቻ መካከል ጣልቃ ገባ:: የምሥራቁን ክፍለ ዓለም የገዛው ፖምፒ የተባለው የጦር ጀነራል፣ ከሦስት ወር ከበባ በኋላ በቤተ መቅደስ በአገልግሎት ላይ የነበሩትን ካህናት በመጨፍጨፍ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገባ:: ይህ በሮማውያን አስተዳደር መጀመሪያ ላይ የተፈጸመው አሰቃቂና አስቀያሚ ድርጊት በአይሁድ ዘንድ የሚረሳና ይቅር የሚባል ሊሆን አልቻለም::

## ሥነ ጽሑፍ

በእነዚህ ደስ በማያሰኙ፣ የውጭና የውስጥ ችግር በነገሠባቸው ዓመታት፣ የአይሁድ ሕዝብ ተጽፈው የተቀመጡና የዘመኑን ሁኔታ የሚያወሱ አዋጋቢ ጽሑፎችን ትተው ዐልፈዋል:: ከነዚህም ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያላቸው ሦስቱ ሥራዎች የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፣ አዋልድ መጻሕፍትና የሙት ባሕር ጥቅልሎች ናቸው::

## የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም፤

የአይሁድ አፈ ታሪክ እንደሚያስረዳው፣ በ250ዓ.ቅ.ክ ገዳማ በበጥሊሞስ ፊላደልፈስ ኀላፊነት፣ 72 ሊቃውንት በአሌክሳንደርያ አቅራቢያ በምትገኘው በፋሮስ ደሴት ላይ፣በ72 ቀናት ውስጥ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ወደ ግሪክ (ጽርእ) ተረጐሙ:: ከዚህ ትውፊት የተነሣ መጽሐፉ ሴፕቱዋጀንት፣ "የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም" ተብሎ ተጠራ:: ስሙን በምኅጻረ ቃል ለመጻፍ የሮማውያንን 70 ቍጥር (LXX) የምንጠቀምበት ለዚህ ነው::

ከትውፊቱም በተጨማሪ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት፣ በእስክንድርያ ይኖሩ ለነበሩት የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ አይሁድ ሲባል ወደ ግሪክ ቋንቋ የተተረጐሙት 250ዓ.ቅ.ክ ላይ ነው የሚል ግምት አለ:: የተቀሩት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትና አዋልድ መጻሕፍት፣ በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ውስጥ የተጨመሩት የክርስትና ሃይማኖት ከመጀመሩ በፊት ነው፤ ነገር ግን የተጻፉበት ዘመን በትክክል አይታወቅም::

የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከፓለስቲና ወጭ፣ እንደ እስክንድርያ ባሉ አካባቢዎች ለሚኖሩትና የአይሁድን ቋንቋ ለማያናገሩት አይሁድ መጽሐፍ ሆነ:: ይህ ትርጒም ያመጣው እሉታዊ ተጽዕኖ ምን ያህል እንደ ሆነ በትክክል ማወቅ ባይቻልም እንኳ፣ የአባቶቻቸውን ቋንቋ መናገር ለማይችሉት አይሁድና የግሪክ ቋንቋ ለሚናገረው ዓለም ተዘጋጅቶ የቀረበ የብሉይ ኪዳን ቅጅ ነበር:: በኋላም መጽሐፉ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ሆነ::

## አዋልድ መጻሕፍት

አዋልድ ስሚለው የግሪኩ አቻ ቃል "አፖክሪፋ" የሚለው ሲሆን ትርጒሙም፣ "የተደበቀ" ማለት ነው:: አዋልድ መጻሕፍት በመባል የሚታወቁት በሁለቱ ኪዳናት መካከል የተጻፉት መጻሕፍት ናቸው:: እነዚህ መጻሕፍት በሮማና በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ፣ እንደ እግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል የመታየታቸው ጒዳይ ውስብስብ የሆነ ታሪካዊ ዳራ አለው::

ዛሬ ፕሮቴስታንቶች የሚቀበሏቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር (የብሉይ ኪዳን ቀኖና) መሠረታቸው የተጣለው ከኢየሩሳሌም ውድቀትና በ70 ዓ.ም ከሆነው ከቤተ መቅደሱ መፍረስ በኋላ በሁለተኛው ምእተ ዓመት መባቻ ላይ ነው::

አይሁድ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ብዛት አስመልክተው፣ እስከ ጀምኒያው ጉባኤ (90ዓ.ም) ድረስ ይወያዩ ነበር:: ይህ የዕብራውያን ቀኖና የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ትጠቀም በነበረው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም:: በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አበው ዘንድ፣ የትኞቹ መጻሕፍት ቀኖናውያት ናቸው፤ የትኞቹ ደግሞ አይደሉም የሚለው ፎአስ ጒዳይ አለመግባባትን ያስከተለ ቢሆንም እንኳ፣ አዋልድ መጻሕፍት እስከ ዘመነ ተሐድሶ ድረስ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ጥቅም ላይ ውለው ነበር:: በዚህ ወቅት አብዛኞቹ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ነባሩን የዕብራውያንን ቀኖና ለመከተል ሲወስኑ፣ የሮማዋ ቤተ ክርስቲያን በትሬንቱ ጉባኤ (1546 ዓ.ም) እንዲሁም በቅርቡ በተካሄደው የመጀመሪያው የቫቲካን ጉባኤ (1869-1870 ዓ.ም) ላይ፣ አዋልድ መጻሕፍትን የሚያጠቃልለውን፣ "የእስክንድርያውን" ቀኖና አጸደቀች::

አዋልድ መጻሕፍትን በመጀመሪያ ይጠቀሙባቸዋው የነበሩት ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ቢሆኑም እንኳ፣ ይህን የሚያደርጉት መጻሕፍቱ ቀኖናውያት ናቸው ብለው አልነበረም::

ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት ከአዋልድ መጻሕፍት ጠቅሰው ማስተማራቸውን የሚያሳይ ግልጽ ማስረጃ የለም (ይሁዳ14 ማብ ይመ)። የጽሑፎቹ ባለቤት የሆነው የአይሁድ ኅብረተ ሰብ ጽሑፎቹን አልተቀበላቸውም። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተመዘገቡት የሐዋርያት ስብከቶች ውስጥ እነዚህ ጽሑፎች የሚሸፍኑት ዘመን ቦታ ሳይሰጠው ተዘሉአል። እንዲያውም እንደ መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ ያሉ መጻሕፍት ብዙ የታሪክ ስሕተትና የጊዜ ቅደም ተከተል መፋለስ አለባቸው።

በቀኖናውያቱ መጻሕፍት የሚካተት፣ ፋይዳ ያለው ትምህርት መለኮት በአዋልድ መጻሕፍት ውስጥ የለም። ይልቁንም ቀኖናውያት የሆኑትን መጻሕፍት የሚጻረሩ ትምህርቶች በአዋልዱ ውስጥ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ፣ አዋልድ መጻሕፍት በሁለቱ ኪዳናት መካከል ያለውን ዘመን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃዎችን የሚሰጡ መሆናቸው መዘንጋት የለበትም።

## የሙት ባሕር ጥቅልሎች

በ1947 ዓ.ም በጸደይ ወራት አንድ ዐረብ እረኛ፣ "የዘመኑ ታላቅ ጽሑፍ ግኝት" ተብሎ የሚጠራው ጥቅልል የተገኘበትን አንድ ዋሻ በሙት ባሕር ዳር ደቡባዊ ምዕራብ አቅጣጫ አየ። በዚህ አካባቢ ባሉ ዋሻዎች የተገኙ፣ "የሙት ባሕር ጥቅልሎች" የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ጥቅልሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን፣ አቡቀለምሲሳዊ ሥራዎችን፣ ጥንታውያን የእምነት ዐርበኞችን ገድል የሚተርኩ ጽሑፎችንና እነዚህን ጽሑፎች ስለ ጻፉ ሰዎች የሚናገሩ ጽሑፎችን የሚያጠቃልሉ ናቸው።

በዚያ ስፍራ የተገኙት ጽሑፎች በግምት የመዝሙረ ዳዊት ሢሶ፣ አሪት ዘዳግም፣ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የሚገኘው ትንቢተ ኢሳይያስና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው። አስደናቂ ከሆኑት ግኝቶች አንዱ 7.30 ሜትር ርዝመት ያለው የኢሳይያስ መጽሐፍ ጥቅልል ይገኝበታል።

እነዚህ ጥቅልሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አጻጻፍ እንዴት እንደ ሆነ ለማወቅ ተነሥቶ ሰነበረው ጥያቄ ዐይነተኛ መልስ ያስገኙ ሲሆኑ፣ ከዚህ በፊት ከሚታወቁት ቅጆች ይልቅ ከመጀመሪያው ጽሑፍ ጋር የ1000 ዓመት ቀረቤታ ያላቸውን ቅጆች የያዙ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸውን የዕብራይስጥና የአራማይክ ቋንቋዎች ለመረዳትና በኪዳናት መካከል የይሁዲነት ዕድገት እንዴት እንደ ነበር ለማወቅ ተችሎአል። ይህ ግኝት ለመጽሐፍ ቅዱስ አንባብያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅጆች እንዴት ባለ ጥንቃቄ እንደ ተገለበጡና፣ በዚህም፣ቅጆቹ ያላቸውን አስተማማኝነት ለመገንዘብ ተጨባጭ መረጃ በመሆን ያገለግላል።

## የኅብረተ ሰብ እድገት

ኢየሱስ በአካል በምድር ሳለ ይታይ የነበረው ይሁዲነት (አይሁዳዊ እምነት) በአብዛኛው በሁለቱ ኪዳናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ በተከሠተው ግፊት የመጣው ለውጥ ውጤት ነው።

## ዝርወተ እስራኤል

በምርኮ ዘመን የጀመረው የእስራኤላውያን መበተን የዘመኑ ጸሓፊ አይሁድ "ምድሩንና ባሕሩን" ሞሉት ብሎ እስከሚናገር ድረስ በፍጥነት ተከናውኖ ነበር።

ከፓለስቲና ውጭ የሚኖሩ፣ ከቤተ መቅደስ አምልኮ የተለዩት አይሁድ የራሳቸውን ሃይማኖታዊ ሥርዐት የቶራን መጽሐፍ በማንበብ፣ በምኩራቦቻቸው በመሰብሰብ ይፈጽሙ ነበር። የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞች ወደ ግሪክ ቋንቋ የተመለሰውን ብሉይ ኪዳን በመጠቀም ለሕዝብ የሚሰጡትን አገልግሎት በተበተኑት እስራኤላውያን መካከል ጀምረዋል።

## ሰዱቃውያን

በፓለስቲና የግሪኩ ዓለም አመለካከት በሰዱቃውያኑ ጉራ እማካይነት ተጽዕኖውን በሰፊው አሳድሮአል። በአብዛኛው የገገር መደብ የሚገኝበት ይህ ጉራ፣ የቤተ መቅደስ አካል ሆኗል፤ ካላቸው የሥልጣን ወንበር የተነሣ የፓለቲካውን ጉዳይ የሚቈጣጠሩ ናቸው።

በቊጥራቸው አነስተኛ ቢሆኑም፣ የፓለቲካ ሥልጣኑን በአብዛኛው የያዙ ስለ ሆኑ የሊቀ ካህንነቱም ሥልጣን ከእጃቸው አይወጣም ነበር። ከቶራ በስተቀር የየትኛውንም ሃይማኖታዊ ጽሑፍ ትምህርት (እንደ ሙታን ትንሣኤ ያለ)፣ በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ውስጥ የማይገኘውን ሁሉ አይቀበሉም።

## ምኩራብ

በምርኮ ዘመን እስራኤል ከቤተ መቅደሱ ተለይታ መንግሥት የሌላትና በአረማውያን ግዞታት አምልኮ የተከበበች ነበረች። አምነቷም ወደ መጥፋት ተቃርቦ ነበር። ይህን በመሰሉ ሁኔታዎች ውስጥ እያሉ በምርኮ ላይ የነበሩ አይሁድ የሃይማኖት ትኩረታቸውን ከአከባቢ ነገሮች ላይ እንሥተው ሳይጠፉ ወደ ቀሩት ነገሮች ማለትም ወደ ቶራና ወደ እግዚአብሔር ሕዝብነታቸው እምነት ራሳቸውን መልሰዋል። ስለ መንግሥታቸው ከማሰብ ይልቅ ስለ ሙሴ ሕግ፣ ስለ መቅደሱ ሥርዐቶች ከማሰብ ይልቅ ስለ ግል መንፈሳዊ ሕይወት ማሰብና መሥዋዕት በማቅረብ ፈንታ ጸሎት ላይ ማተኮር ጀመሩ።

ከምርኮ በሚመለሱበት ጊዜ ይህን አዲስ የአምልኮ ዘይቤና በምኵራብ የመሰብሰብ ልማድ ይዘው መጡ፤ ይሁዲነቱም ቶራ ባለበት ስፍራ ሁሉ የሚተገበር ሆነ። የምኵራብ አምልኮ ዐይነተኛ ባሕርይ የሆነው በግል መንፈሳዊ ሕይወት ላይ እና ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ኅብረት ላይ ማተኮር ይሁዲነት እንዳይጠፋ መርዳት ብቻ ሳይሆን፣ ለወንጌልም ጥርጊያ መንገድ አዘጋጅቶአል።

**ፈሪሳውያን**

ፈሪሳውያን የምኵራብ አለቆች የነበሩ ሲሆን የሙሴ ሕግጋትን ለመተርጐም የሚጥሩ ናቸው። ከሙሴ ዘመን እንሥቶ በፍጥነት እየተለዋወጠ በመጣው ዓለም ውስጥ አይሁድ በእግዚአብሔር ፊት የቅድስና ሕይወት እንዲኖራቸውና ሕጉ እንዳይበረዝ የራሳቸውን ሀጥር አበጅተውለት ነበር። ምንም እንኳ ቍጥራቸው አነስተኛና በብሔራዊ ጕዳይ ውስጥም ድርሻ ያልነበራቸው ቢሆኑም፣ ሐሳባቸው በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ነበረው። በ70 ዓ.ም. ቤተ መቅደሱ ሲፈርስ የቀሩት እነርሱ ብቻ ሲሆኑ፣ የዘመናዊው ይሁዲነት መንፈሳውያን አባቶች ናቸው።

**ኤሴናውያን**

የሙት ባሕር ጥቅልሎች እስከ ተገኙበት ጊዜ ድረስ ተረስቶ የቈየ የአይሁድ ክፍል
ሲሆን፣ በመቃብያን ዘመን በተፈጠረው ቅራኔ ራሳቸውን የለዩ አነስተኛ ቍጥር ያላቸው ሰዎች ቡድን ነበር። እንደ ፈሪሳውያን ሕግን መጠበቅ አስፈላጊ እንደ ሆነ ቢያምኑም፣ በቤተ መቅደሱ ያለው ክህነታዊ አገልግሎት የተበላሸ እንደ ሆነ ይቈጥራሉ፤ የመቅደሱንም ሥርዐትና መሥዋዕት ማቅረቡንም አይቀበሉም ነበር። በእያሌ የጥንት ጸሐፍት እንደ ተገለጸው ትክክለኛው የኤሴናውያን ባሕርይ ባይታወቅም የሙት ባሕር ጥቅልሎች በመባል የሚታወቀውን ያዘጋጀው የቍምራን ማኅበረ ሰብ የኤሴናውያን ቡድን እንደ ሆነ የሚጠቁም አጠቃላይ ስምምነት አለ።

ኤሴናውያን እውነተኞቹ ትሩፋን እነርሱ እንደ ሆኑ ስለሚያምኑ፣ በአብዛኛው ራሳ ቸውን ከይሁዲነት ለይተው ስግል መንፈሳዊ ሕይወት ንጽሕናና "የብርሃን ልጆች ከጨለማ ልጆች"ጋር ለሚያደርጉት የመጨረሻ ጦርነት ራሳቸውን የሚያዘጋጁ ነበሩ። ቀደምት "የ ጽድቅ መምህሮቻቸውን" በመመልከት ከአቡቀለምሲሳዊ የእምነት ልምምዳቸው የተነሣ የሁለት ወይም የሦስት መሲሖችን መምጣት ይጠባበቁ ነበር። ሆኖም በ70 ዓ.ም. የሆነው የቤተ መቅደሱ መፍረስ ተስፋቸው የተሟጠጠ እንዲመስል አድርጎታል።

የቍምራን ማኅበረ ሰብን እምነቶች ከክርስትና እምነት ጅማሬ ጋር እኩል ለማድረግ ሙከራዎች ተደርገዋል። አንዳንዶች ኢየሱስን "የጽድቅ መምህሮቻቸው" አምሳያ እንደ ሆነ አድርገው ይወስዱታል፤ እንዲያውም መጥምቁ ዮሐንስንና ኢየሱስን በዚህ ቡድን ውስጥ አባላት እንደ ሆኑ ይቈጥራሉ። ሆኖም ለእነዚህ ግምቶች ትክክለኛ ማረጋገጫ የለም።